legal aiddc

# የቤት ውስጥ ጥቃት ከደረሰብዎ እና የጥበቃ ትዕዛዝ ያገኙ ከሆነ፣ በዋሽንግተን ዲሲ ውስጥ የክራይ ውልዎን እንዴት ማቋረጥ እንደሚችሉ

ዲሲ ውስጥ የሚኖሩ ከሆነ እና የቤት ውስጥ ጥቃት ስለደረሰብዎ የጥበቃ ትዕዛዝ ያለዎት ከሆነ፣ የክራይ ውልዎን ሳይጠናቀቅ የማቋረጥ መብት አለዎት። **የክራይ ውልዎን ሳይጠናቀቅ ለማቋረጥ ስለፈለጉ የቤት አከራይዎ *ገንዘብ ሊያስከፍልዎ ወይም ተቀማጭ ገንዘብዎን ለመቁረጥ አይፈቀድለትም* ።**

ሶስት ቅደም ተከተሎችን በመከተል የክራይ ውልዎን ሳይጠናቀቅ ያቋርጡ፦

**ቅደም ተከተል 1፦** ወደሚቀጥለው ገጽ ይሂዱ እና ዓባሪ የተደረገውን ደብዳቤ ይሙሉ።
*ይሄ ደብዳቤ የቤት ክራይ ውልዎን እያቋረጡ እንደሆነ ለአከራይዎ ያሳውቃል። የእርስዎን ተቀማጭ ገንዘብ መያዝ እንደማይችሉ ያሳውቃቸዋል። ለእርስዎ (ተከራይ) እና ለእርስዎ አከራይ አንዳንድ መሰረታዊ መረጃ ማከል ያስፈልጎታል።*

**ቅደም ተከተል 2፦ ለአከራይዎ ደብዳቤውን <u>እና</u> የጥበቃ ትዕዛዙን ቅጂ ይላኩ።**
*ኢሜይል ሊያደርጉት፣ በደብዳቤ ሊልኩት ወይም በአካል ሊሰጧቸው ይችላሉ። ማስታወሻ፦ ቅጂውን ይያዙ። ኦርጅናሉን የጥበቃ ትዕዛዝ አሳልፈው **እንዳይሰጡ** (በዳኛው የተፈረመበት)።*

**ቅደም ተከተል 3፦ አስተማማኝ የሆነ አድራሻ አንዴ ካገኙ በኋላ፣ የተቀማጭ ገንዘብዎ የሚልኩበት አስተማማኝ አድራሻ ለአከራይዎ ይንገሯቸው።**

**ይሄ ላይ ምን ያህል መስራት አለብኝ?** የክራይ ውልዎን ጊዜው ሳይጠናቀቅ እንደሚያቋርጡ ለአከራይዎ ለመንገር ክስተቱ ሪፖርት ከተደረገበት ቀን ጀምሮ **90 ቀናት** (ወደ 3 ወር ) ገደማ አለዎት።

*የቤት አከራይዎ ገንዘብ ሊያስከፍልዎ ወይም ተቀማጭ ገንዘብዎን ሊያስቀር የሚሞክር ከሆነ፣ ሕግ እንደጣሱ ሊቆጠር ይችላል። የቤት አከራይዎ ምን እንደሚያደርጉ ጥያቄ ያለዎት ከሆነ፣ በ (202)-628-1161 ላይ ሌጋል ኤድ ጋር ይደውሉ ወይም ወደዚህ ይሂዱ www.legalaiddc.org/online-intake።*

*የጥበቃ ትዕዛዝ የሌለዎት ከሆነ እና ማግኘት የሚፈልጉ ከሆነ፣ ዲሲ ሴፍ (DC SAFE) ን በ (844) 443-5732 ላይ ደውለው ያግኙ ወይም የዲሲ የቤት ውስጥ ጥቃት ፍርድ ቤት ክፍል ቢሮን (D.C. Court Domestic Violence Division Clerk's office) (202) 879-0157 ላይ ደውለው ያግኙ*

***እገዛ ይፈልጋሉ?*** *(202) 628-1161 ላይ ሌጋል ኤድ ጋር ይደውሉ ወይም ወደዚህ ይሂዱ www.legalaiddc.org/online-intake/።*

______________________________________
የእርስዎ ስም

______________________________________
የእርስዎ የደብዳቤ አድራሻ

______________________________________
ቀን

______________________________________
የቤት አከራዩ ስም ወይም የቤት አቅራቢው ስም

______________________________________
የእርስዎ ቤት አከራይ የደብዳቤ አድራሻ

ጉዳዩ፡ <u>በዲሲ ደንበ ሕግ § 42-3505.07 መሰረት የቤት ክራይ ውል የማቋረጥ ማስታወቂያ</u>

ውድ የቤት አቅራቢ፡-

እኔ፣ ___________________________፣ ይሄንን ደብዳቤ የምጽፈው በእኔ የተከራየሁበት ቤት ቁጥር ____________________ ላይ ያለኝን የክራይ ውል የማቋረጥ ፍላጎት እንዳለኝ በመደበኛ ሁኔታ ለማሳወቅ ነው። በዲሲ ሕገ ደንብ § 42-3505.07 መሰረት፣ ያለምንም የቅጣት ክፍያ ማሳወቂያ በደረስዎ አስራ አራት (14) ቀናት ውስጥ የእኔን የክራይ ውል ማቋረጥ ይጠበቅቦታል ምክንያቱም፡-

1. በዲሲ ሕገ ደንብ ቁጥር § 16-1001(8) መሰረት የቤት ውስጥ ጥቃት ተጠቂ ነኝ፣ እና
2. በዲሲ ሕገ ደንብ ቁጥር § 16-1005 መሰረት የጥበቃ ትዕዛዝ አለኝ (ቅጂው ዓባሪ ተደርጓል)።

በዲሲ ሕገ ደንብ ቁጥር § 42-3505.07 መሰረት፣ ፣ ከሁለቱ የትኛው ቀድም አንዱ ቢመጣም፣ ከዛሬ ጀምሮ የሚቆጠር ለ 14 ቀናት ያህል ውጪ የቤት ክራይ ሊያስከፍሉኝ **አይችሉም** ወይም የቤት ክራዩን ለሌላ ሰው ማከራየት አይችሉም። የክራይ ውሉን ጊዜው ከመጠናቀቁ በፊት ስላቋረጥኩኝ ተቀማጭ ገንዘቤን መቁረጥ **አይችሉም**። ዲሲ ሕገ ደንብ § 42-3505.07 *ይመልከቱ*። ተቀማጭ ገንዘቡን ለእኔ መልሰው እንዲልኩልኝ የሚልኩበት አድራሻ አሳውቆታለሁኝ።

ማንኛውም ዓይነት ጥያቄዎች ያለዎት ከሆነ፣ እባክዎን በዚህ አድራሻ ያግኙኝ ___________________________። እናመሰግናለን።
ስልክ ወይም የኢሜይል አድራሻ

ከአክብሮት ጋር፣

______________________________________
ፊርማ (የተከራይ ፊርማ)

**በተጨማሪም በደብዳቤ ውስጥ፡-** የፍትሃብሔር ጥበቃ ትዕዛዝ ቅጂ